# የዮሐንስ ራእይ ጥናት



አድነው ተሾመ

**በቅርቡ የሚታተም...**

**© Global Good News Mission 2023**

# የዮሐንስ ራእይ ጥናት

**አድነው ተሾመ**

**2023 ዓ.ም. (እ.ጎ.አ.)**

**የዮሐንስ ራእይ ጥናት**
**©2023 አድነው ተሾመ**
**Cover picture by Goodsalt - used by permission**
**Copyrighted pictures within the book – used by permission**
Artwork by Pat Marvenko Smith, ©1982/1992 - www.revelationillustrated.com

# ማሳሰቢያ

ይህንን መጽሐፍ ወይም በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምስሎች ያለ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ ወይም በከፊል ማባዛት፣ መገልበጥ፣ መቅረጽ፣ በማንኛውም መገናኛ ብዙኃንም ሆነ ማኅበራዊ ሚዲያ ማሠራጨት አይፈቀድም። ሆኖም ለቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም ሆነ ለማስተማሪያነት መጥቀስ ቢፈለግ የመጽሐፉን ርእስና ደራሲውን በመጥቀስ መጠቀም ይቻላል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት የዘመን አቆጣጠሮች በሙሉ እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር እንደ ሆኑ ማሳሰብ እወዳለሁ። በተጨማሪም፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች በሙሉ (ምኀጻረ ቃል ካልተጨመረባቸው በስተቀር) በዋናነት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1962 ዓ.ም. በታተመው ነባሩ ትርጉም ነው። ለጥናት እንዲያመች በማለት፣ በየምዕራፎቹ መጀመሪያ ላይ፣ የራእይን መጽሐፍ ጥናት ክፍል በ1962 ዓ.ም. በታተመው በነባሩ ትርጉምና በአዲሱ መደበኛ ትርጉም (አ.መ.ት.)፣ ለንባብ እንዲረዳ በማለት ጎን ለጎን እንደ መግቢያ አስቀምጠናል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ላሉት አንዳንድ መረጃዎች የድህረ ገጽ (website) ማጣቀሻዎች *በዋቢ መጻሕፍትና የድረ ገጽ ማጣቀሻዎች* በሚለው የመጽሐፉ መጨረሻ ክፍል ላይ አስቀምጠናል። አንዳንድ ድህረ ገጾች ከነበሩበት ሥፍራ ሊቀየሩ ወይም ሊጠፉ ስለሚችሉ፣ በዚያ መረጃ ዙሪያ ኢንተርኔት ላይ ፍለጋ ብታደርጉ ተመሳሳይ መረጃ (ማጣቀሻ) ማግኘት ትችላላችሁ።

ምላስ ምግብን፣ ጆሮ ቃልን (ድምጽን) እንደሚያጣጥሙ፣ ዐይን ደግሞ ኅብረ ቀለማትን ስለሚያጣጥም፤ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ሥዕሎችና ሥዕላዊ መግለጫዎች በውበት እንዲቀርቡ ለማድረግና ለመጽሐፉ ተነባቢነት እንዲያግዝ መጽሐፉን ሙሉ ለሙሉ በተለያዩ ቀለማት አድርጌዋለሁ። በየምዕራፎቹ መግቢያዎች ላይ ካሉት የራእይ ንባብ ክፍሎች በስተቀር፣ ከእግዚአብሔር ቃል የተጠቀሱ ጥቅሶች በሙሉ በቀይ ቀለም ናቸው።

# ምሥጋና

ከሁሉ በፊት ይህንን ከባድ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በትኩረት አጠና ዘንድ ልቤን ያነሣሣውን እግዚአብሔርን ማመስገን እወዳለሁ።

ሆኖም፣ ያለ እግዚአብሔር ቤተሰቦች ደግሞ ሙሉ የሆነ ነገር መሥራት ስለማይቻል፣ እግዚአብሔርም በአብዛኛው ቸርነቱንና በጎነቱን የሚገልጽልን በእግዚአብሔር ሰዎች በኩል ስለ ሆነ፣ ይህ መጽሐፍ በዚህ መልኩ ለተደራስያን እንዲቀርብ አስተዋጽዖ ያደረጉትን ወገኖች ማመስገን እወዳለሁ።

ከእነዚህም መካከል መጽሐፉ ገና ለቅድመ አንባቢያንም ከመድረሱ በፊት ሳዋየው፣ "መጀመሪያ በደንብ ደጋግመህ በማንበብ አመንኸኸው" በማለት በጣም ጠቃሚ ምክር የመከረኝን ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁንን ማመስገን እወዳለሁ። የራሱን ተሞክሮ በማከል፣ የሚከተለውን ምክር አካፈለኝ፤ አንድ ጊዜ፣ በየጊዜው እየተሰበሰቡ መጽሐፍ ለሚገመግሙ ወገኖች መጽሐፌን ስሰጣቸው፣ "እንግዲህ፣ መጽሐፉ ታትሞ ያለቀለት ስለ ሆነ፣ 'ደራሲው ሞቶአል' ብለን ነው የምንገመግመው" አሉኝ፣ አለ። እኔም፤ "ደራሲው ሞቶአል" ተብዬ ከመገምገም ለመዳን የተቻለኝን ለማድረግ ሞክሬአለሁ። በተጨማሪም፣ "መጽሐፍህን የቻልኩትን ያህል አይቼዋለሁ። በጣም ጥሩና ብዙ የተደከመበት ሥራ ነው። ከእኔ በላይ በራእይ መጽሐፍ ላይ ብዙ ያስተማረና መጽሐፍም የጻፈ ጓደኛዬን ዶ/ር አዳም ቱሉን እንዲያየው ሰጥቸዋለሁ።" በማለት ከዶ/ር አዳም ቱሉ ጋር በማስተዋወቅ ጠቃሚ ሐሳቦችንና እርምቶችን እንዳገኝ ረድቶኛል። ዶ/ር አዳም ቱሉንም በዚህ አጋጣሚ ከልብ አመሰግናለሁ።

ከቅድመ አንባቢያን መካከል በመጀመሪያ መጥቀስ የምፈልገው፣ የራሴ ፓስተር የሆነውንና የምወደውን መጋቢ (ዶ/ር) ኃይሉ ቸርነትን ነው። ፓስተር ኃይሉ ሥራው ሁሉ ጥርት ያለ ነው። እኔም የዚህ ጸጋ ተካፋይ ስለ ሆንሁኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ቀጥሎም በቅድመ አንባቢነት መጽሐፉን አንብበው የሚያንጽ ምክር፣ እርማትና ማበረታቻ የሰጡኝን፣ መጋቢ/ቄስ (ዶ/ር) ቶለሳ ጉዲናን፣ መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳንን፣ ወንድም ንጉሤ ቡልቻን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌን፣ ቄስ (ዶ/ር) ኪሮስ ላቀውን፣ ከልብ ማመስገን እወዳለሁ።

ይህንን የራእይን ጥናት በማካሂድበት ጊዜ፣ ወንድም ምኒሊክ አስፋው፣ ለጥናቴ የሚረዱኝን በራእይ መጽሐፍ ላይ የሚያተኩሩ አንዳንድ መጻህፍትን በPDF መልክ ስለላከልኝ 'ጌታ ይባርክህ' ማለት እወዳለሁ። ወንድም ምኒሊክ የአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ በሚተረጎምበት ጊዜ የራእይ መጽሐፍ ትርጓሜ ላይ ብዙ አስተዋጽዖ ያደረገ ወንድም እንደሆነ ተረድቻለሁ። በራእይ መጽሐፍ ዙሪያ በውስጡ ያለውን የከበረ መረዳት በጽሑፍ ሊያቀርብልን እንዲችል ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት ጸሎቴ ነው።

# ከቅድመ አንባቢያን

የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ ለማየት እድሉን በማግኘቴ ደስ መሰኘቴን አልሸሽጋችሁም። ይህ መጽሐፍ ራእይን በግል ለማጥናት ከተደረገ ጥረት የተወለደ መሆኑን ከጥንስሱ አውቃለሁ። በመደበኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ሳያልፉ ቃሉን ሰዎች ቢጠሙ ጥረታቸው የት ድረስ ይዟቸው እንደሚሄድ ተግባራዊ ምሳሌን አሳይቶኛል። ከዚህ አኳያ ልፋት ለውጤት ድካም ለስኬት ሲበቃ በማየቴ ደስ ብሎኛል። በተጨማሪም ምስጢራዊና አስቸጋሪ የሆነውን ይህንን አይነኬ መጽሐፍ ቀለል ባለ ቋንቋ ለማስረዳት የተደረገው ጥረት የሚበረታታ ነው። ከለት ተለት ኑሯችንም ጋር ተዛማጅነቱን በአያሌ ክፍሎቹ ስለሚያሳይ ለመንፈሳዊ እርምጃችን እገዛው በቀላሉ አይታይም። መጽሐፍ ቅዱስን መደበኛ በሆነ ሁኔታ ላልተማሩ አማንያን ብቻ ሳይሆን በመለስተኛ ደረጃ እየተማሩም ላሉ ሥራው ዐይን ከፋች ነው። ራእይ መጽሐፍን ለመረዳት የሚያግዝ አንድ ተጨማሪ ድጋፍ ነው። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የጥናት ቡድኖች ውስጥ ለጥናት ግልጋሎት ላይ ቢውልም ገምቢ ነው። በሚያቀርበውም ትንተና እና ገለጣ ለእውቀት ለውጥ ብቻ ሳይሆን የሕይወት ለውጥ እንዲገኝ ስለሚጎተጉት ራስንም ለማየት እድል ይሰጣል። በመሆኑም የማዕዱ ተቋዳሽ ለመሆን ገዝታችሁ ብታነቡት ታተርፉላችሁ።

መጋቢ ኃይሉ ቸርነት (ዶ/ር)
በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ዋና መጋቢ

---

የራእይ መጽሐፍ ጥልቅ የሆኑትን መልእክቶች ያዘለ ስለ ሆነ በቀላሉ አንብቦ መረዳትና ለዕለታዊ ክርስቲያናዊ ኑሮ ለመጠቀም ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነው። ወንድማችን አድነው ተሾመ እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ በዚህ የራእይ መጽሐፍ ጥናት ብዙ ምርምር አድርጎ ከሌሎችም ጥናቶች ጋር በማገናዘብ እጅግ የሚደንቅ መጽሐፍ፣ ማንም ሰው አንብቦ በሚረዳ መልኩ ለአንባቢያን አቅርቧል። ይህ የራእይ መጽሐፍ ጥናት በአንድ ጊዜ ተነቦ የሚዘለቅና የሚረሳ ሳይሆን፣ በዝግታ ከቀን ወደ ቀን በጸሎት መንፈስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጋር ማዋሀድ፣ በመጽሐፉ መጀመሪያ (ራእይ 1÷3) ላይ የተገባውን የበረከት ተስፋ ቃል ወራሽ ያደርጋል። የራእይን መጽሐፍ በጥልቅ ለማወቅና ከበረከቱ በሙላት ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ሁሉ ይህን መጽሐፍ በጥናታቸው ውስጥ ቢጨምሩ ትልቅ አስተዋጽዖ ያደርጋል ብዬ ከልቤ በማመን ሁሉም ገዝተው እንዲጠቀሙበት የእግዚአብሔርን ሕዝብ አበረታታለሁ።

ቄስ ቶለሣ ጉዲና (ዶ/ር)
የአትላንታ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና መጋቢ

---

*የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ጥናት* የተሰኘው ይህ መጽሐፍ፣ ልክ እንደ ስሙ ነው። በብዙዎች የማይደፈረውን 66ኛውን «ቅዱስ መጽሐፍ» ለራሳቸው ለመረዳትም ሆነ ለሌሎች ለማስረዳት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ ከመጽሐፉ - ከራሱ - ቀጥሎ፣ *የራእይ መጽሐፍ ጥናት* በእጅጉ ጠቃሚ ግብዓት እንደሚሆናቸው እርግጠኛ ነኝ። ከቅርጹ (form) የይዘቱ (content)፣ ከይዘቱ የተደራሽነቱ (accessibility)። ትንሹም፣ ትልቁም ሳይቸከባቸው፣ ይልቁንም እየጣፈጣቸው፣ ያጠኑበታል። ጸሐፊው ሲያስብበት እና ሲዘጋጅበት ረዥም ጊዜ እንደ ቆየ ሌላ ምስክር አያሻውም። ከልብ

የሆነው ምኞቴ፣ ከእያንዳንዱ አማኝ/አገልጋይ የመጻሕፍት መደርደሪያ ላይ፣ ለሁሉ እንደሚታይ፣ ሆኖ እንዲቀመጥ ነው። ወንድሜ አድነው፣ ጌታ ብ-ር-ክ ያድርግህ!

በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)

---

ይህ የዮሐንስ ራእይ ጥናት አካታችነቱና ቅልብጭነቱ አስደሳች ነው። ወንድሜ አድነው ተሾመ አነጋጋሪ የሆኑትን ልዩ ልዩ ምንባቦች በጥንቃቄና በሰከነ ተጠየቃዊ አካሔድ ይተነትናል። የራሱን አቋም ይገልጥልናል፤ ሌሎች አቋሞች የሉም አይለንም። ለጥናት የተመቸ፣ ለማስተማር በሚረዳ ግልጽ አቀማመጥ የተረደፈ (በረድፍ የተቀመጠ)፣ በዐይነ ግቡ ሥዕሎችና ሠንጠረዦች የታገዘ ጥሩ ሥራ ነው።

መምሕር ንጉሤ ቡልቻ
የቀድሞ የቃለ እግዚአብሔር ማኅበር ዳይሬክተር

---

ወንድማችን አድነው ተሾመ እንደ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር፣ ረጅም ዓመት የራእይ ዮሐንስን መጽሐፍ አጥንቶአል። በዚህ አግባብ ይህ መጽሐፍ የረጅም ዓመት፣ አስተውሎ ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ይህ ሲባል ግን፣ ሰው ሁሉ የትርጓሜውን አካሄድ በአሜንታ ይቀበላል ማለት አይደለም። በዐሳብ ገበያው ላይ ካሉ ንድፈ ዐሳቦቹ መኻል አንዱን ወይም ሁለቱን አካሄድ ያስተዋውቃል። ትርጓሜውን ከዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ለማዛመድ ጥረት ያደርጋል። ለነገረ መለኮት ማበብ እንዲሁም የእግዚአሔርን ዐሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለመረዳት ለሚሹ የሚሆን ሥራ ነው።

ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ
የተስፋ ዐቃብያን ክርስትና ማኅበር መሥራችና የሰሜን አሜሪካ ቢሮ ዳይሬክተር

---

የተዘጋጀውን የጥናት መጽሐፍ ጊዜ ወስጄ ያነበብኩት ሲሆን የራዕይን መጽሐፍ ሚስጥራዊ አባባሎች የገለጠ፣ በደንብ ያብራራና ማንም የራዕይን መጽሓፍ ለማጥናት ለሚፈልግ አሰተዋጽአው ከፍተኛ ሆኖ አግኝቸውአለሁ። ደግሞም የዚህ እጅግ ሚስጥራዊ መጽሐፍ ፍቺ ከግለሰብ ግላዊ ቅድመ ግንዛቤ አሰተሳሰብ ነጻ በሆነና የመጽሐፉ ሚሥጥረ ፍቺ በራሱ በመጽሓፉ፣ በብሉይና አዲስ ኪዳን ዋቢ መጻሕፍት የተፈታ መሆኑ ተአማኒነቱን ከፍተኛ አድርጎታል። ሰለ ሆነም የጥናት መጽሐፉን በቂ ጊዜ ወስዶ በጥንቃቄ ያዘጋጀውን ወንድም አድነው ተሾመን ጌታ ይባርክህ እያልኩኝ በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የራዕዩን መጽሐፍ በግል፣ በቡዱን፣ በማህበራነ ምእመናን፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እና ለመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች ማሰተማሪያም ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደ ሆነ በማመን እንድንጠቀምበት መልእክቴ ነው።

ቄስ ኪሮስ ላቀው (ዶ/ር)
የኢ.ወ.ቤ.ክ. መካነ ኢየሱስ ም/ፕሬዚደንት እና የአዲስ አበባ ሲኖዶስ ፕሬዚደንት

---

# የዮሐንስ ራእይ ጥናት

## ማውጫ

መቅድም፤
........................................................................................................ 7
መግቢያ፤
........................................................................................................ 9
ምዕራፍ አንድ
የራእይ መጽሐፍ ዳሰሳ፤........................................................................ 11
ምዕራፍ ሁለት
የክርስቶስ በክብር መገለጥ፤ (ራእይ 1)................................................ 24
ምዕራፍ ሦስት
ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤ (ራእይ 2-3)............................................ 49
ምዕራፍ አራት
በዙፋኑ ላይና በዙፋኑ ዙሪያ፤ (ራእይ 4)............................................ 104
ምዕራፍ አምስት
በሰባት ማኅተም የተዘጋው መጽሐፍና በጉ፤ (ራእይ 5)........................ 114
ምዕራፍ ስድስት
ሰባቱ ማኅተሞች፤ (ራእይ 6).............................................................. 123
ምዕራፍ ሰባት
መቶ አርባ አራት ሺህ መታተማቸውና ነጭ ልብስ የለበሱ፤ (ራእይ 7)............... 147
ምዕራፍ ስምንት
ሰባተኛው ማኅተምና፤ ሰባቱ መለከቶች፤ (ራእይ 8)................................ 158
ምዕራፍ ዘጠኝ
አምስተኛውና ስድስተኛው መለከቶች - ሁለቱ ወዮዎች፤ (ራእይ 9) .................. 166
ምዕራፍ ዐሥር
ትንሿ መጽሐፍ፤ (ራእይ 10)................................................................ 178
ምዕራፍ ዐሥራ አንድ
ሁለቱ ምስክሮችና ሰባተኛው መለከት፤ (ራእይ 11)................................ 185
ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
ሴቲቱና ታላቁ ቀይ ዘንዶ፤ (ራእይ 12)................................................ 203
ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት
ሁለቱ አውሬዎች፤ (ራእይ 13)............................................................ 216
ምዕራፍ ዐሥራ አራት
በጉ፤ መቶ አርባ አራት ሺዎቹና የምድር መከር መታጨድ፤ (ራእይ 14)........... 243
ምዕራፍ ዐሥራ አምስት
የመጨረሻውን መቅሰፍቶች የያዙ ሰባቱ መላእክት፤ (ራእይ 15)...................... 259

ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

የመጨረሻው መቅሰፍት የሞላባቸው ሰባቱ ጽዋዎች፤ (ራእይ 16)..................... 265

ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

በአውሬው ላይ የተቀመጠችው ሴት፤ (ራእይ 17)............................................ 275

ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

የታላቂቱ ከተማ የባቢሎን ውድቀትና ፍርድ፤ (ራእይ 18)...................................291

ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

የበጉ ሰርግ እና የክርስቶስ ዳግም ምጽአት፤ (ራእይ 19)........................................302

ምዕራፍ ሃያ

የክርስቶስ ሺህ ዓመት ንግሥ፤ (ራእይ 20).........................................................328

ምዕራፍ ሃያ አንድ

አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፤ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፤ (ራእይ 21 – 22÷5)..........341

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

እነሆ በቶሎ እመጣለሁ! (ራእይ 22÷6–21).........................................................362

ዋቢ መጻሕፍትና የድረ ገጽ ማጣቀሻዎች ........................................................................372

# መቅድም

ጌታን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ከተቀበልሁበት ከ1974 ዓ.ም. ጀምሮ፣ “ሥራዬ” ብዬ ይህንን የራእይ መጽሐፍ ያጠናሁበት ጊዜ አልነበረም። ማንበብና ማጥናት ትልቅ ልዩነት አለው። ማንበብ ከሆነ በተደጋጋሚ ጊዜያት አንብቤዋለሁ፤ ነገር ግን በልዩ ትኩረት ላጥና ብዬ ሳጠናው ይህ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው። ይህም ከመሬት ተነሥቶ አይደለም፣ “መፈለግንም ማድረግንም በእኛ ውስጥ የሚሠራ” ጌታ፣ ይህንን መጽሐፍ እንዳጠና ከ2019 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ ፍላጎትን በውስጤ በልዩ መንገድ አስቀመጠ። ልቤም አእምሮዬም ወደዚህ መጽሐፍ እንደ ማግኔት ተሳበ።

በብዙዎቻችን ዘንድ ይሄ መጽሐፍ አይነኬ ስለ ሆነ፣ ከሁሉ በፊት፣ “ጌታ ሆይ! ይህንን መጽሐፍ በሚገባ እንድረዳ እርዳኝ፣ አንተ ራስህ አስተምረኝ” በማለት መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረኝ መጸለይ ጀመርሁኝ። ከዚያም ደጋግሜ መጽሐፉን ማንበብ፣ ማጥናትና ማሰላሰል ጀመርሁ። ስለ ራእይ መጽሐፍ የተጻፉ ጥቂት የማይባሉ መጻሕፍትን በማሰባሰብ፣ የተለያዩ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ከግንዛቤ ለማስገባት የተቻለኝን ያህል ጥረት አድርጌአለሁ። እነዚህን የተለያዩ አመለካከቶች ከቃኘሁ በኋላ፣ በልቤ ሰክኖ ያገኘሁትን ለራሴ ብይዝም፣ ከእናንተ ጋር አብረን በምናደርገው ጉዞ ግን፣ ያሉትን የተለያዩ አመለካከቶች ለእናንተ በማቅረብ፣ የራሴንም ግንዛቤ ግልጽ በማድረግ፣ እያንዳንዳችሁ በውስጣችሁ ባለው መንፈስ ቅዱስ የራሳችሁን ግንዛቤና ድምዳሜ እንድትደርሱ በትሕትና ማሳሰብ እወዳለሁ። ከዚህ በፊት ከነበራችሁ አመለካከት ለየት ያለ ነገር ቢያጋጥማችሁም፣ በልበ ሰፊነት እንድትመለከቱት በትሕትና እጠይቃለሁ።

ይህንን መጽሐፍ በ2021 ላይ ጨርሼ በ2022 አሳትማለሁ ብዬ በዝግጅት ላይ እያለሁ፣ እኔ አባል የሆንኩባት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆነው መጋቢ ዶ/ር ኃይሉ ቸርነት፣ መጽሐፉን እንዲያዩልኝ ከሰጠኋቸው ቅድመ አንባብያን አንዱ ስለ ነበረ፤ በሎስ አንጀለስ በምትገኘው የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን በእሑድ ማለዳ የሰንበት ትምህርት የራእይን መጽሐፍ እንዳስተምር ስለ ጠየቀኝ፤ ከDec 2021 ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል ሳስተምረው ቆየሁ። ይህም የጌታ ዓላማ እንደ ነበረ ተረድቻለሁ። የራእይን መጽሐፍ ጥናት የበለጠ ለራሴም ቢሆን እንደገና እንዳብላላው በጣም ረድቶኛል።

ይህንን መጽሐፍ እዚህ ለማድረስ በወሰደው ረጅም የጥናት ጉዞ፣ ጳውሎስ በአንደኛ ቆሮንቶስ 13÷12 *“ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፣ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ ዐውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ ዐውቃለሁ።”* እንዳለ፣ ማንም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ ነኝ ቢል፣ ሁሉን ነገር በግልጽ አውቄአለሁ ማለት እንደማይችል ተረድቻለሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት፣ ‘አንቱ’ የተባሉት የመጽሐፍ ቅዱስና የሥነ መለኮት አስተማሪዎች፣ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ብዙ ትንታኔ ሲሰጡ አስተውያለሁ። የእነርሱን ተቃራኒ አመለካከቶች ስናነብ በእውነትም በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ለመረዳት አያዳግትም። የእኔ ምክር፤ ይህንን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ ከሁሉ በላይ

በውስጣችሁ ያለው መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምራችሁ በጸሎት መንፈስ በመሆን፣ ከዚህ በፊት የነበራችሁ መረዳት ብቸኛውና ትክክለኛው እውነት ነው ብሎ ግትር ባለማለት፣ *"ነገሩ እንዲህ ይሆንን?"* ብለው ቃሉን ይመረምሩ እንደ ነበሩት ልበ ሰፊ የቤሪያ ሰዎች፣ በልበ ሰፊነት እንድታነቡና እንድታጤኑት በትሕትና አሳስባለሁ።

# መግቢያ

የራእይ መጽሐፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት መጽሐፍት ሁሉ ለማንበብና ለመረዳት ብዙ ጥረት የሚጠይቅና ብዙዎች ለማንበብ የማይደፍሩት መጽሐፍ ነው። ስለ መጨረሻው ዘመን የሚናገር፡ ብዙ ምልክቶችና ተምሳሊቶች ባሉበት የአጻጻፍ ዘይቤ የተጻፈ ትንቢታዊ መጽሐፍ ስለ ሆነ፣ በንጽጽር እንደ ሮሜ መልእክት ሰተት ብሎ የሚገባ መልእክት ወይም መጽሐፍ አይደለም። ስለዚህም በብዙዎች ዘንድ አይደፈርም።

በ2ኛ ጴጥሮስ 1÷20 *"ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም።"* ስለሚል፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት መልእክቶችም ሆኑ ትንቢቶች እንደ መሰለን የምንተረጉማቸው አይደሉም። የሚያስገርመው ነገር፣ ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ይልቅ፣ የራእይን መጽሐፍ የሚያነብም ሆነ ሲነበብ የሚሰማ፣ "ብጹዕ" ወይም "የተባረከ" እንደ ሆነ የተጻፈለት መጽሐፍ ነው። በአንጻሩ ደግሞ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፈው ለሚጨምርም ሆነ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፈው ለሚያጎድል ታላቅ ማስጠንቀቂያ የተጻፈበት መጽሐፍ ነው።

*"ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።" ራእይ 1÷3*
*"እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ። የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ።" ራእይ 22÷7*
*"በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።" ራእይ 22÷18-19*

ከላይ የተጻፉትን የበረከት ተስፋ ቃሎችና ከባድ ማስጠንቀቂያዎች ስናነብ፣ በአንድ በኩል ይህንን መጽሐፍ በማንበብ፣ በመስማትና በመጠበቅ ያለውን በረከት ለመቀበል በመጓጓት፣ በአንጻሩ ደግሞ የተሰጠውን ታላቅ ማስጠንቀቂያ ከግንዛቤ በማስገባትና በመጠንቀቅ፣ ይህንን መጽሐፍ ለማንበብና ለማጥናት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ልባችን ሊነሳሳ ይገባዋል። በተለይም፣ በዓለም ዙሪያ በየቀኑ የምናየውና የምንሰማው ነገር፣ የዓለም መጨረሻና የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በደጅ እንደ ሆነ የሚያሳዩ ምልክቶች እንደ ደመና በዙሪያችን ከብበውን ያለበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን መልእክቶች ማንበብና በተቻለን መጠን መረዳት ለተያያዝነው የእምነት ጉዞ ታላቅ ግብዓት፣ ስንቅና ትጥቅ ይሆነናል።

ይህንን መጽሐፍ፣ ለግልም ሆነ ለቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ላላችሁ ለጥናታችሁ እንደ አንድ የጥናት መጽሐፍ ወይም ማጣቀሻ (Reference) እንድታውሉት በትኅትና አበረታታለሁ።

# ምዕራፍ አንድ
# የራእይ መጽሐፍ ዳሰሳ

## የዚህ መጽሐፍ ስያሜ

ይህ መጽሐፍ በአማርኛ "የዮሐንስ ራእይ" ሲባል፣ ከራእይ 1÷1 ከግሪኩ የመጀመሪያው ቃል ላይ የተወሰደ፣ Apokalypsis (Ἀποκάλυψις) የሚል ቃል ነው። የግሪኩ ቃል ሁለት ክፍል ሲኖረው፣ 'Apo'–'ማስወገድ' ወይም 'ማንሳት' ማለት ሲሆን፣ 'kalypsis' ደግሞ 'መሸፈን' ወይም 'መክደን' ማለት ነው። የጥምሩ ቃል 'Apokalypsis' ትርጓሜ፣ "ሽፋኑን ማንሳት" ወይም መግለጥ፣ "የተገለጠ" ወይም "ሽፋኑ የተነሳ" ማለት ነው።[1] አንድ ሙሽራ የሙሽሪትን ቬሎ ሲያነሳ/ሲገልጥ እንደ ማለት ነው። አፖካሊፕሲስ የሚለውን የግሪክ ቃል አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ 'አቡቀለምሲስ' ብለውታል።[2]

"ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም **የተገለጠው** ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥" ራእይ 1:1

## የራእይ መጽሐፍ ደራሲ ማነው? የተጻፈውስ መቼ ነው?

የራእይ መጽሐፍ ጸሐፊ ሐዋርያ ብሎ እራሱን ባይጠራም፣ ራሱን ዮሐንስ ብሎ በተደጋጋሚ በምዕራፍ 1 ቁ 1፣ 4፣ እና 9 እንዲሁም በምዕራፍ 22 ቁ 8 ላይ ያስተዋውቃል።

*"እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና መንግሥቱን የኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግሥት የምካፈል ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ።"* (ራእይ 1÷9)

በማለት ሐዋርያው ዮሐንስ እንደ ሆነ የሚጠቁሙ ነገሮችን ይነግረናል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም፣ በመጀመሪያዎቹ ምዕተ ዓመታት ከነበሩት የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጀምሮ፣ ከዚያም በኋላ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ (ከጥቂት የእምነት አባቶች በስተቀር) የሐዋርያው ዮሐንስን ደራሲነት ተቀብለውታል።[3]

ይህ መጽሐፍ የተጻፈበትን ጊዜ በተመለከተ፣ አብዛኛዎቹ የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን አባቶችም ሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ መለኮት ዐዋቂዎች እንደሚስማሙበት በ95 እና 96 ዓ.ም. አካባቢ እንደ ሆነ ብዙዎች የሚቀበሉት ሐሳብ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት እንዲጋዝ ያደረገው፣ ከ81–96 ዓ.ም. የሮማ ገዥ የነበረው ንጉሥ ዶሚሽያን (Emperor Domitian) በ96 ዓ.ም. ሲሞት፣ ዮሐንስ ከፍጥሞ ደሴት ግዞት በዚያኑ ዓመት እንደ ተመለሰ ይታመናል።[3a] ሆኖም፣ ጥቂቶች፣ የተጻፈው ከ54–68 ዓ.ም. ገዥ ከነበረው ከኔሮ በኋላ በ68-69 ዓ.ም. ነው የሚሉም አሉ።[3b] በተለይ በውስጡ ያለው ትንቢታዊ መልዕክት ስለ መጨረሻው ዘመን

ሳይሆን፣ በ70 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ላይ ስለ መጣው ጥፋት የሚተርክ ነው ብለው የሚያምኑ ጥቂት ሰዎች የተጻፈው በ68-69 ዓ.ም. ነው የሚለውን ሐሳብ ያራምዳሉ።

## የመጽሐፉ ዋና ዐላማና መልእክት

የመጽሐፉ ዋና ዐላማ፣ በምዕራፍ 1፥1 *"ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ..."* እንደሚል፣ የእግዚአብሔር ባሪያዎች በሙሉ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዙሪያ ሊሆኑ ያሉትን ነገሮች ያውቁና ይዘጋጁ ዘንድ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም በኩል ለሐዋርያው ዮሐንስ የተገለጸ ራእይ ነው።

በዐጭሩ፣ ይህ የራእይ መጽሐፍ "የመጨረሻው ዘመን ወይም የነገረ-ፍጻሜ" ትምህርት (Eschatology) ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ነው። በማቴ 24፥3 *"…. የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው?"* ብለው ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን እንደ ጠየቁትና፣ እርሱም ምልክቶቹን እንደ ነገራቸው ሁሉ፣ በዚህ መጽሐፍ ደግሞ፣ ማንም ሰው ጠይቆት ሳይሆን፣ ይህንን መረዳት እንደሚያስፈልገን እግዚአብሔር ስለሚያውቅ፣ *"ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥"* (ራእይ 1፥1) ይለናል።

## የራእይ አተረጓጎም በዘመናት

ባለፉት 2000 ዓመታት፣ የራእይን መጽሐፍ ሰዎች በተለያየ መንገድ ሲተረጒሙት ኖረዋል። እነዚህ አመለካከቶች በአራት ዋና ዋና መንገዶች ይከፈላሉ። ከእነዚህ አራት መንገዶች ሁለቱን አመለካከቶች በመቀላቀል ቅይጥ የሆነ አመለካከት ያላቸውም አሉ። እነዚህ አራት ዋና ዋና አመለካከቶች የሚከተሉት ናቸው። [4]

### 1. ወደ ፊት ላይ ያተኮረ (ትንቢታዊ) አመለካከት (Futurist)

ይህ አመለካከት፣ ከራእይ ምዕራፍ 1 እስከ 3 በስተቀር፣ ከምዕራፍ 4 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 22 ድረስ ያለው ሁሉ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በሚደርስበት ጊዜና ከዚያም ባሻገር የሚሆነውን የሚናገር ትንቢታዊ ቃል ነው የሚል አመለካከት ነው። ይህ አመለካከት፣ መሉ በሙሉ በሚባል መልኩ በቀድሞዩቱ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ተይዞ የነበረ፣ አሁንም በአብዛኛው ወንጌላዊያን አማኞች ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው። በዚህም መጽሐፍ የምንጋራው ይህንን አመለካከት ነው። የሚቀጥሉትን ሦስት አመለካከቶች የምናቀርበው፣ በዘመናት፣ የተለያዩ ሰዎች የተከተሏቸውን የተለያዩ አመለካከቶች ከግንዛቤ እንድታስገቡ በማለት ብቻ ነው እንጂ ጊዜ ወስደን በጥልቀት እንድናያቸው አይደለም።

### 2. ታሪካዊ አመለካከት (Historicist)

ይህ አመለካከት፣ በራእይ መጽሐፍ ያሉት መልእክቶች በአብዛኛው በታሪክ የተፈጸሙ ናቸው የሚል ነው። ይህንን አመለካከት የጀመረው አንድ ከ1135 እስከ 1202 ዓ.ም. የነበረ ኢዮአቄም (Joachim of Floris) የሚባል መነኩሴ ሲሆን፣ የራእይን መጽሐፍ፣ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እርሱ እስከ ነበረበት ዘመን ድረስ የሚናገር ታሪክ ተኮር የሆነ መጽሐፍ እንደ ሆነ አድርጎ ይተረጉም ነበር። በተለይ 1260 ቀናት ተብሎ በራእይ መጽሐፍ በተደጋጋሚ የተጻፈውን፣ አንዱን ቀን በአንድ ዓመት በመውሰድና 1260 ዓመታት በማድረግ፣ እርሱ በነበረበት ዘመን፣ ዘመኑ ሊያልቅ እንደ ደረሰ የሚናገር ሰው ነበረ። ይህ አተረጓጎሙ፣ አመታቱ ደርሰው ሲያልፉ በገሃድ ስህተት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ከእርሱ በኋላም በየዘመናቱ ታሪካዊ አተረጓጎሙን በተለያየ መንገድ እየለዋወጡ የሚያቀርቡ እስከ አሁንም ድረስ አሉ።

## 3. በኀላፊ ጊዜ የሚታይ ወይም የተፈጸመ (Preterist)

ይህ አመለካከት፣ በራእይ መጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ራዕዩ ወደ ዮሐንስ በመጣ ጊዜ ስለ ነበሩና ከዚያ በፊትም ስለ ተፈጸሙ ጉዳዮች የሚናገር እንጂ ገና ወደ ፊት የሚፈጸም አይደለም የሚሉ ናቸው። በራእይ ያለው ትንቢት ሁሉ በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በጠፋችበት ጊዜ የተፈጸሙ ናቸው ብለው ያምናሉ። ለዘብ ያሉት ደግሞ፣ ከ70 ዓ.ም. በኋላ በታሪክ የተፈጸሙ ክስተቶችንም ያጠቃልላል በማለት “ከታሪካዊ አመለካከት” ጋር በመቀየጥ፣ አንዳንዶቹም “ከትንቢታዊ አመለካከት” ጋር በመቀየጥ ወደ ፊት የሚከሰቱ ትንቢቶች እንዳሉም የሚያምኑ አሉ። በአጠቃላይ፣ የራእይ መልእክት፣ በዚያን ጊዜ በስደት ላይ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለማጽናናት የተጻፈ ገለጻ (descriptive) እንጂ ትንቢታዊ (predictive) አይደለም የሚል አመለካከት አላቸው።

## 4. ምሳሌአዊ (ተምሳሌታዊ) እና ሥዕላዊ (Idealist-Symbolical)

ይህ አመለካከት፣ የራእይ መጽሐፍ ትንቢታዊም ሆነ ታሪካዊ ትርጒም እንደሌለው፣ ነገር ግን በምሳሌአዊና በሥዕላዊ መግለጫ፣ በክፉና በደግ፣ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ያለውን ፍልሚያ ትምህርታዊ በሆነ መንገድ የሚያሳይ ነው ይላል።

# የመጽሐፉ ቅንብር (አከፋፈል)

የራእይ መጽሐፍን አከፋፈል፣ ከራሱ ከመጽሐፉ ከምዕራፍ 1 ቍጥር 19 ላይ እናገኛለን።

**“እንግዲህ ያየኸውን፣ አሁንም ያለውን፣ ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።”**

1. ያየኸውን

2. አሁንም ያለውን
3. ከዚህም በኋላ **ይሆን ዘንድ** ያለውን

**ያየኸውን፣**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዮሐንስ *'ያየኸውን'* ሲለው፣ ከራእይ 1፥9-20 የትንሳኤው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዮሐንስ አይቶ በማያውቀው ክብር፣ ሞገስና ግርማ ተገልጾለት ያየውን የጌታን ክብር ማለቱ ነው።

**አሁንም ያለውን፣** ሲል

በራእይ ምዕራፍ 2 እና 3 በዚያን ጊዜ በእስያ ለነበሩት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የመጣላቸውን መልእክት የሚያመለክት ነው።

**ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን፣** ሲል ደግሞ፣

ከራእይ ምዕራፍ 4 ጀምሮ እስከ ራእይ ምዕራፍ 22 ለዮሐንስ የተገለጸውን፣ በራእይ 1፥1 *"ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን …"* የተባለለትን የፍጻሜ ነገሮች የሚያመለክት ነው። እንዲሁም፣ በራእይ 4፥1 *"….ወደዚህ ውጣና **ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን** ነገር አሳይሃለሁ"* በማለት ወደ ፊት ሊሆን ያለውን እንደሚያሳየው ይነግረናል።

## የዮሐንስ ራእይ አከፋፈል ዘርዘር ባለ መልኩ

| | |
|---|---|
| **ምዕራፍ 1፥1-8** | መግቢያና ሰላምታ |
| **ምዕራፍ 1፥9-20** | ክርስቶስ በታላቅ ክብር ሲገለጽ |
| **ምዕራፍ 2 እና 3** | ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላከ መልእክት |
| **ምዕራፍ 4** | በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ያለው ታላቅ ክብርና አምልኮ |
| **ምዕራፍ 5** | በሰባት ማኅተም የተዘጋው መጽሐፍ፣ ማኅተሙን ሊፈታ የተገባው የይሁዳ አንበሳና የታረደው በግ |
| **ምዕራፍ 6** | የስድስቱ ማኅተሞች መፈታት |
| **ምዕራፍ 7** | በምድር፣ ከእስራኤል ነገድ 144,000 መታተምና፣ በዙፋኑ ፊት ደግሞ፣ ከነገድና ከቋንቋ ስፍር ቍጥር የሌላቸው፣ ከታላቁ መከራ የወጡ፣ ነጭ የለበሱ ሕዝቦች። |

| | |
|---|---|
| **ምዕራፍ 8 እና 9** | የሰባተኛው ማኅተም መፈታት፣ (የግማሽ ሰዓት ዝምታ) ሰባቱን መለከቶች የያዙ መላእክትና ከሰባቱ ስድስቱ መለከቶች መነፋት |
| **ምዕራፍ 10** | ትንሿ መጽሐፍና ሰባቱ ነጎድጓዶች |
| **ምዕራፍ 11** | ሁለቱ ምስክሮችና ሰባተኛው መለከት |
| **ምዕራፍ 12** | ታላቅ ምልክት በሰማይ፣ ሴቲቱና ቀዩ ዘንዶ |
| **ምዕራፍ 13** | ከባህርና ከምድር የወጡት ሁለት አውሬዎች (ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ነቢይ) እና 666 |
| **ምዕራፍ 14** | በጉ በጽዮን ተራራ ከታተሙት 144,000 ጋር፤<br>በምድር ሊሆን ያለው ታላቅ ቍጣ፤ የምድር መከር መታጨድና የወይን ዘለላው ተቆርጦ በእሳት ውስጥ መጣል፤ |
| **ምዕራፍ 15 እና 16** | ሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች፣ (የእግዚአብሐርን ቍጣ የተሞሉ ሰባቱ ጽዋዎች) |
| **ምዕራፍ 17 እና 18** | የታላቂቱ አመንዝራ (ታላቂቱ ባቢሎን) ፍርድ |
| **ምዕራፍ 19** | ታላቂቱ አመንዝራ ስለ ተፈረደባት በሰማይ ታላቅ ምሥጋና፣ የበጉ ሰርግ፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የዓለም መንግሥታት ፍጻሜ |
| **ምዕራፍ 20** | የክርስቶስ ሺህ ዓመት ንግሥ፣ የመጨረሻው ፍርድና የዲያብሎስ ፍጻሜ |
| **ምዕራፍ 21፥1 - 22፥5** | አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፤ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ መውረድና የዘላለም ንግሥና |
| **ምዕራፍ 22፥6 - 21** | መደምደሚያ |




*ከእንግሊዝኛ የተተረጎመ (http://www.middletownbiblechurch.org/newtesta/ntesta13.htm)

በራእይ 5፣ በሰባት ማኅተም የተዘጋውን መጽሐፍ ለመዘርጋትና ሰባቱን ማኅተሞች ለመፍታት የተገባው የይሁዳ አንበሳና የታረደው በግ፣ በሰባት ማኅተም የታተመውን የመጽሐፍ ጥቅልል፣ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከእግዚአብሔር አብ ቀኝ እጅ ሲወስድ እናያለን።



ከሰባቱ ማኅተሞች ስድስቱ በራእይ ምዕራፍ 6 ሲፈቱ እናነባለን። በራእይ ምዕራፍ 8፥1 *"ሰባተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።"* ካለ በኋላ ወዲያው በራእይ 8፥2 "በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው" ይላል። ሰባተኛው ማኅተም፣ ሰባቱን መለከቶች የሚያስጀምር ይመስላል። እንደዚሁም፣ በራእይ 11፥15 ሰባተኛው መለከት ሲነፋ፣ *"የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል"* የሚል ታላቅ ድምፅ ከሰማይ ይሰማል። ከዚያም በራእይ 11፥18 ላይ *"ቍጣህ መጣ… ምድርንም የሚያጠፉትን ልታጠፋ ዘመን መጣ"* በማለት የእግዚአብሔር የመጨረሻ ቍጣ በምድር ላይ እንደሚመጣ ያውጃል። ይህም የሆነው፣ ሰባተኛው መለከት የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያውጅና ከምጽዓቱ ጋር ተያይዞ አስቀድሞ የሚመጡትን ሰባት የእግዚአብሔር ቍጣ የሞላባቸውን ጽዋዎች ወደ ምድር መፍሰስ የሚያስጀምር ምልክት ስለ ሆነ ነው ይላሉ። እነዚህን ሦስት 'ሰባቶች' በምናይበት ጊዜ፣ ሰባተኛው ማኅተም፣ ሰባቱን መለከቶች፤ ሰባተኛው መለከት ደግሞ ሰባቱን ጽዋዎች የሚያውጁ ይመስላል። በሰባቱ ማኅተም የተዘጋው መጽሐፍ፣ ሦስቱንም 'ሰባቶች' በውስጡ ያካተተ መጽሐፍ ነው ማለት እንችላለን።

የሰባቱን ማኅተሞች፣ ሰባቱን መለከቶችና ሰባቱን ጽዋዎች ቅደም ተከተልና ግንኙነት በተመለከተ ሁለት አመለካከቶች አሉ።

አንደኛው አመለካከት፤ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን፣ ሰባተኛው ማኅተም ሰባቱን መለከቶች፣ ሰባተኛው መለከት ደግሞ ሰባቱን ጽዋዎች እንደሚያስጀምር የሚያሳይ ነው። ከዚህ በታች ያለው ስዕላዊ መግለጫ ይህንን አመለካከት ያሳየናል።




ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ፤

ማኅተሞቹን በተመለከተ የመጀመሪያው አራት ማኅተሞች ሲፈቱ፣ አራቱ የፈረስ ጋላቢዎች (ነጩ፣ ቀዩ፣ ጥቁሩና ግራጫው ፈረሶች) በቅደም ተከተል ከወጡ በኋላ፣ አምስተኛው ማኅተም ሲፈታ፣ በምድር ላይ የሚከናወን ክሥተት ሳይሆን፣ "ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ።" (ራእይ 6÷9) በማለት፣ በሰማይ የሚከናወን እንደ ሆነ ይገልጽልናል።

ስድስተኛውን ማኅተም በተመለከተ ደግሞ፣ "[12]ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥ [13]በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፥ [14]ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ ዐለፈ፥ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ። [15]**የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለ ጠጋዎችም ኃይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች ዓለቶች ተሰወሩ፥ [16]ተራራዎችንና ዓለቶችንም፡- በላያችን ውደቁ በዙፋንም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቍጣ ሰውሩን፤ [17]ታላቁ የቍጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።"** (ራእይ 6÷12-17) በማለት፤ በማቴ. 24 ላይ ጌታ በመጨረሻው ዘመን እርሱ ሊመጣ ሲል የሚታዩትን ምልክቶች የሚመስሉ ምልክቶችን የሚያሳይ ነው።

ስድስተኛው ማኅተም በእውነትም የመጨረሻውን የበጉን ቍጣ የሚገልጽ ነው። ሰባተኛው ማኅተም ደግሞ በራእይ 8÷1 በተፈታ ጊዜ፣ "እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ" ይላል። ስለዚህ፣ ስድስተኛው ማኅተም በምድር ላይ የመጨረሻውን የእግዚአብሔርን ቍጣ የሚያሳይ ስለ ሆነ፣ ሰባተኛው ማኅተም ደግሞ በእግዚአብሔር ቁጣ ጊዜ በሰማይ የሚከሰተውን

ጸጥታ የሚያሳይ ስለ ሆነ፣ ስድስተኛውና ሰባተኛውን ማኅተም ወደ መጨረሻ አድርገው፣ ሰባቱን መለከቶች የሚያስጀምሩት ከአራቱ ፈረሰኞች (ከአራተኛው ማኅተም) በኋላ ነው።

እንደዚሁም ስድስቱ መለከቶች ከተነፉ በኋላ፣ ሰባተኛው መለከት በራእይ 11÷15 ላይ ሲነፉ "በሰማይም፣ የዓለም መንግሥታት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፣ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል" ስለሚል፣ ሰባተኛውም መለከት ስለ መጨረሻው የክርስቶስ ንግሥና ነው የሚናገረው። ይህንን ተከትሎ፣ ጽዋዎቹን በራእይ 16 በምድር ላይ ሲያፈሱ የሚገልጸውን ክፍል፣ ወደ ኋላ መለስ በማድረግ፣ ጽዋዎቹን ከአራተኛው መለከት በኋላ ያስጀምሯቸዋል። ይህ አመለካከት የመጨረሻዎቹን **ሰባተኛ ማኅተም፣ ሰባተኛ መለከትና ሰባተኛ ጽዋ፣** ከክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ጋር በማያያዝ፣ በአንድ የፍጻሜ ጊዜ መስመር ላይ በማድረግ በሚቀጥለው መልክ ይገልጹታል። [5]




ይህንን ከላይ ያለውን አመለካከት በደንብ ያስተዋልኩት፣ ይህንን መጽሐፍ ጽፌ በክለሳ ላይ እያለሁና፣ የራእይን መጽሐፍ ለአንድ ዓመት በሎስ አንጀለስ በምትገኘው የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን የማለዳ የሰንበት ትምህርት በማስተማር ላይ እያለሁ ነበር። ለአንድ ዓመት ትምህርቱን በማስተምርበት ጊዜ ለራሴም እንደገና ብዙ ነገሮችን እንዳጤንና እንዳመነኘግ ዕድል ስለ ሰጠኝ የነበሩኝን አንዳንድ መረዳቶች እንዳጎለብት ረድቶኛል። በተለይ ስድስተኛውን ማኅተም እያነበቡ፣ ከክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ማለት ይከብዳል። ሰባቱን ማኅተሞች፣ ሰባቱን መለከቶችና፣ ሰባቱን ጽዋዎች ስንመለከት፣ ሙሉ ለሙሉ አንዱ ከሌላው ተከትሎ የሚጀምር (sequential) ናቸው፤ ለማለትም ሆነ፣ ሙሉ ለሙሉ ተደራራቢ (parallel) ናቸው፤ ለማለት አስቸጋሪ ነው። ከተጠቀሱት ሁለት የጊዜ ፍሰቶች ውስጥ ሁለተኛው የበለጠ ትክክለኛ ይመስለኛል። ማን መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ ማለት ይችላል?

## ሦስቱ ወዮዎች፤

*ከአራቱ መለከቶች በኋላ፣ የሚቀሩትን ሦስት መለከቶች በተመለከተ፤*

*"አየሁም፥ አንድም ንስር በሰማይ መካከል እየበረረ በታላቅ ድምፅ፦ ሊነፉ ያላቸው የሦስቱ መላእክት መለከት ስለሚቀረው ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩት **ወዮላቸው፥ ወዮላቸው፥ ወዮላቸው** ሲል ሰማሁ። " ራእይ 8÷13*

ወዲያውኑ፣ አምስተኛው መለከት ይነፋል፤

**“የመጀመሪያው ወዮ” → 5ተኛው መለከት (ራእይ 9÷1-11) – 5 ወራት የሚቆይ ክፉ ቁስል**

*“ሰዎችም ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም…” ራእይ 9÷6*

“ፊተኛው ወዮ አልፏል፤ እነሆ ከዚህ በኋላ ገና ሁለት ወዮ ይመጣል።” ራእይ 9÷12

**“ሁለተኛው ወዮ” → 6ተኛው መለከት (ራእይ 9÷13-21)**

ቁ. 15 ***“የሰዎችንም ሲሶ እንዲገድሉ*** *ለሰዓቱና ለቀኑ ለወሩም ለዓመቱም ተዘጋጅተው የነበሩ አራቱ መላእክት ተፈቱ”*

*ራእይ 11÷14 “እነሆ ሁለተኛው ወዮ አልፏል እነሆ ሦስተኛው ወዮ በቶሎ ይመጣል”*

**“ሦስተኛው ወዮ” → 7ተኛው መለከት ፡- ሰባቱን መቅሰፍቶች የሚያውጅ**

*ራእይ 11÷15 “ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም፣ የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል፣ የሚሉ ታላላቅ ድምጾች ሆኑ።”*

*በራእይ 11÷18 ላይ* ***“ቊጣህ መጣ…*** *ምድርንም የሚያጠፉትን ልታጠፋ ዘመን መጣ”*

*ሦስተኛው ወዮ፣ ከስድስተኛው መለከት በኋላ የሚመጡት፣ በእነርሱም የእግዚአብሔር ቊጣ የሚገለጽባቸው ጽዋዎች ናቸው ማለት እንችላለን።*

# ሰባቱ ማኅተሞች

ራዕይ 6 እና 8፡1-2

| 1ኛ ማኅተም | 2ኛ ማኅተም | 3ኛ ማኅተም | 4ኛ ማኅተም | 5ኛ ማኅተም | 6ኛ ማኅተም | 7ኛ ማኅተም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ነጭ ፈረስ | ቀይ ፈረስ | ጥቁር ፈረስ | ግራጫ ፈረስ | የሰማዕታት ጩኸት | ምልክቶች በሰማይ | የመጨረሻው መጀመሪያ |
|  |  |  |  |  |  |  |
| ራዕይ 6፡2<br>አየሁም፥ እነሆም፥ አምባላይ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት ነበረው፥ አክሊልም ተሰጠው፥ ድልም እየነሣ ወጣ ድል ለመንሣት። | ራዕይ 6፡4<br>ሌላም ዳማ ፈረስ ወጣ፤...ሰላምን ከምድር ይወስድ ዘንድ ሰዎችም እርስ በርሳ ቸው እንዲተራረዱ ሥልጣን ተሰጠው፤ ታላቅ ሰይፍም ተሰጠው | ራዕይ 6፡5-6<br>በእርሱም ላይ የ ተቀመጠው በእጁ ሚዛን ያዘ። አንድ እርቦ ስንዴ በዲናር ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፥ | ራዕይ 6፡8 በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው። | ራዕይ 6፡9-11<br>ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ።....እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። | ራዕይ 6፡12-17<br>ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ ....ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? | ራዕይ 8፡1-2<br>እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ። በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ፥ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው። |

# ሰባቱ መለከቶች

**ራዕይ 8፣ 9 እና 11**



1ኛ ቆሮ 15:51-52



| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| ደምም የተቀላቀ ለበት በረዶና እሳት ሆነ፥ ወደ ምድርም ተጣለ፤ የምድርም ሲሶው ተቃጠለ የዛፎችም ሲሶው ተቃጠለ የለመለመም ሣር ሁሉ ተቃጠለ። | በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ የባሕርም ሲሶው ደም ሆነ፤ በባሕርም ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሲሶው ሞተ የመርከቦችም ሲሶው ጠፋ። | እንደ ችቦም የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፥ በወንዞችና በውኃም ምንጮች ሲሶ ላይ ወደቀ። የኮከቡም ስም እሬቶ ይባላል። የውኃውም ሲሶ መራራ ሆነ መራራም ስለ ተደረገ በውኃው ጠንቅ ብዙ ሰዎች ሞቱ። | የፀሐይ ሲሶና የጨረቃ ሲሶ የከዋክብትም ሲሶ ተመታ፥ የእነዚህ ሲሶ ይጨልም ዘንድ፥ የቀንም ሲሶው እንዳያበራ እንዲሁም የሌሊት | የጥልቁንም ጉድጓድ ከፈተው፤ ጢስም ከታላቅ እቶን እንደሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጉድጓዱ ወጣ ከጢሱም አንበጣዎች ወደ ምድር ወጡ፥ የምድርም ጊንጦች ሥልጣን እንዳላቸው ሥልጣን ተሰጣቸው። በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም፥ | የሰዎችንም ሲሶ እንዲገድሉ ለሰዓቱና ለቀኑ ለወሩ ለዓመቱም ተዘጋጅተው የነበሩ አራቱ መላእክት ተፈቱ።...ከአፋቸውም በወጡት በእሳቱና በጢሱ በዲኑም በእነዚህ ሦስት መቅሰፍቶች የሰዎቹ ሲሶ ተገደለ። | የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል፤... ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ...ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ። |
| **ራዕይ 8:7** | **ራዕይ 8:8-9** | **ራዕይ 8:10-11** | **ራዕይ 8:12** | **ራዕይ 9:1-11** (የ5 ወራት ሥቃይ) | **ራዕይ 9:13-21** | **ራዕይ 11:15-19** የምጽዓቱና የቀጣው ጊዜ ደረሰ |

# የእግዚአብሔር ቁጣ የሞላባቸው ሰባቱ ጽዋዎች

## ራዕይ 15 & 16



| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |   |   |  |
| ፊተኛውም ሄዶ ጽዋውን በምድር ውስጥ አፈሰሰ፤ የአውሬውም ምልክት ባለባቸው ለምስሉም በሚሰግዱ ሰዎች ክፉኛ የሚነዘንዝ ቍስል ሆነባቸው። | ሁለተኛውም ጽዋውን በባሕር ውስጥ አፈሰሰ፤ እንደ ሞተም ሰው ደም ሆነ፥ በባሕር ከሚኖሩት ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ። | ሦስተኛውም ጽዋውን በወንዞችና በውኃ ምንጮች ውስጥ አፈሰሰ፤ እነርሱም ደም ሆኑ። | አራተኛውም ጽዋውን በፀሐይ ላይ አፈሰሰ፤ ሰዎችንም በእሳት ልታቃጥል ተሰጣት። ሰዎችም በታላቅ ትኵሳት ተቃጠሉ፥ | አምስተኛውም ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ መንግሥቱም ጨለማ ሆነች ከስቃይም የተነሳ መላሶቻቸውን ያኝኩ ነበር፥ | ስድስተኛውም ጽዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው ውኃው ደረቀ።...በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲ ያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ። | ሰባተኛውም ጽዋውን በአየር ውስጥ አፈሰሰ፤ ከመቅደሱም ውስጥ 'ተፈጽሞአል' የሚል ታላቅ ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ። |
| ራዕይ 16:2 | ራዕይ 16:3 | ራዕይይ 16:4 | ራዕይ 16:8-9 | ራዕይ 16:10-11 | ራዕይ 16:12-16 | ራዕይ 16:17-21 |

ሙሉ መጽሐፉን ለማግኘት ያግኙን

info@globalgoodnews.org
adntesh@gmail.com
(323)868-3202

# ምዕራፍ ሁለት

# የክርስቶስ በክብር መገለጥ

በራእይ ምዕራፍ 1 ላይ የመጽሐፉን መግቢያ፣ ሰላምታ እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክብርና ግርማ ለዮሐንስ ሲገለጥ እናያለን።

## መግቢያና ሰላምታ

**ራእይ 1፥1-8**

<table>
<tr><th>በ1962 የታተመው የድሮው ትርጒም</th><th>አዲሱ መደበኛ ትርጒም</th></tr>
<tr>
<td>የዮሐንስ ራእይ 1<br>1 ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥<br>2 እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ።<br>3 ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።<br>4-5 ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤ ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፥ ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኵር የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥<br>6 መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኀይል ይሁን፤ አሜን።<br>7 እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዐይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።<br>8 ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፡- አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።</td>
<td>1 ቶሎ መሆን የሚገባውን ነገር ለአገልጋዮቹ እንዲያሳይ፣<br>እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ<br>ራእይ ይህ ነው፤ ኢየሱስም መልአኩን ልኮ ለአገልጋዩ<br>ለዮሐንስ ገለጠለት፤ 2 እርሱም ስለ እግዚአብሔር ቃልና<br>ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ያየውን ሁሉ<br>መሰከረ። 3 ዘመኑ ቀርቦአል፤ እንግዲህ ይህን የትንቢት<br>ቃል የሚያነብ ብፁዕ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንም<br>የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው። 4 ከዮሐንስ፤<br>በእስያ አውራጃ ለሚገኙ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤<br>ካለው፣ ከነበረውና ከሚመጣው፣<br>በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፣<br>1፥4 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ 5 እንዲሁም ታማኝ<br>ምስክር፣ ከሙታን በኵርና የምድር ነገሥታት ገዥ<br>ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋና ሰላም ለእናንተ<br>ይሁን። ለወደደንና ከኀጢአታችንም በደሙ ነጻ<br>ላወጣን፣ 6 አምላኩንና አባቱን እንድናገለግልም<br>መንግሥትና ካህናት ላደረገን፣ ለእርሱ ክብርና ኀይል<br>ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁ አሜን። 7 እነሆ፤ በደመና<br>ይመጣል፤<br>የወጉት እንኳ ሳይቀሩ፣ ዐይን ሁሉ ያየዋል፤ የምድርም<br>ሕዝቦች ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ዋይ ዋይ ይላሉ።<br>አዎ! ይህ ሁሉ ይሆናል፤ አሜን።<br>8 “ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም፣<br>ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ፣ አልፋና ዖሜጋ<br>እኔ ነኝ” ይላል።</td>
</tr>
</table>